# የይስማዕከ ወርቁ «ራማቶሓራ» 40 ሺ ኮፒ ታተመ

---------------------------------------------------------------

*አዲስ አድማስ*

«ዴርቶጋዳ» በተሰኘ የመጀመሪያ ረቅም ልቦለድ መጽሐፉ ተወዳጅነት ያገኘው ይስማዕከ ወርቁ ሰሞኑን ያወጣው ሁለተኛ ክፍል ልቦለድ መጽሐፍ 40ሺ ኮፒ እንደታተመ ተገለፀ፡፡ «ዴርቶጋዳ» 10 ጊዜ የታተመ ሲሆን ከ130 ሺ ኮፒ በላይ ታትሞ መሰራጨቱን የአዲስ አድማስ ምንጮች ጠቁመዋል፡፡

የደራሲው ሁለተኛ ክፍል የመፅሃፉ ረቂቅ ባልታወቁ ግለሰቦች መዘረፉን ደራሲው መግለፁ የሚታወስ ሲሆን፣ ቀደም ሲል በቁርጥራጭ ወረቀቶችና ማስታወሻዎች ላይ በሰፈሩ ታሪኮች ታግዞ ልቦለዱን በድጋሚ እንደፃፈው ገልጿል፡፡ ረቂቁ ከጠፋ በኋላ እንደገና መፃፍ አስቸጋሪ እንደነበር የተናገረው ደራሲው፤ ታሪኩን መጀመሪያ ስፅፈው በደንብ ስላብላላሁትና ከ«ዴርቶጋዳ» የሚቀጥሉ ገፀ ባህርያት ስላሉበት በፍጥነት በድጋሚ ለመፃፍ አግዞኛል ብሏል፡፡

በጠፋው ታሪክና በድጋሚ በተፃፈው መካከል አንዳንድ ልዩነቶች እንዳሉ በመጥቀስ አሁን በታተመው ላይ ቀድሞ ያልነበረ «አርባጫ» የተባለ ገፀ ባህሪ እንደተጨመረ፣ የጠፋው ረቂቅ በ33 ምዕራፍ የተከፈለ ሲሆን የአሁኑ በ40 ምዕራፍ መከፈሉን ደራሲው ለአዲስ አድማስ ገልጿል፡፡

«ዴርቶጋዳ» የዚህንያህል ተወዳጅ ይሆናል ብዬ አላሰብኩም ነበር ያለው ይስማዕከ፤ አዲሱ ሥራው እንደቀድሞው ተወዳጅነት ያገኛል አያገኝም የሚለውን መናገር ይከብደኛል ብሏል፡፡

«እኔ የምፈልገውን ፅፌአለሁ፤ ፍርዱ የአንባቢው ነው» በማለት፡፡ ደራሲው «ተልማድ» የተሰኘ ሌላ ልብወለድ ለህትመት እንዳዘጋጀ ገልጿል፡፡ የሩሲያ ደራሲያንን የልቦለድ ሥራዎች ማንበብ እንደሚመርጥ የተናገረው ይስማዕከ ወርቁ፤ «የወንድ ምጥ» እና «የቀንድ አውጣ ኑሮ» በተሰኙ የግጥም መፃህፍቱም ይታወቃል፡፡